# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

# ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 11-20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከጃንዋሪ 21-31 እና ከፌብርዋሪ 1-10/ 2025

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2025

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ


እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ....- 1 -

ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ....- 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 2 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ....- 2 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....- 2 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 3 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 3 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 4 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ....- 5 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31, 2025 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ....- 5 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....- 5 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 6 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 6 -


እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 6 -




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

በጃንዋሪ የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በተለይም በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ ተጠናክሮ ተስተውሏል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአንዳንድ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም በአዴት 4.2፤ በአዲግራት 4.5፤ በሐሮማያ 4.8 1.8፣ 3.8፣ 3.0፣ 1.6፣ 1.8፣ -0.4፤ በአለም ከተማ 4.8፣ 1.8፣ 3.8፣ 3.0፣ 1.6፣ 1.8፣ -0.4፤ በአምባማሪያም 4.0፣ 3.6፣ 3.6፣ 4.8፣ 4.5፤ በአርሲ ሮቤ 4.0፣ 4.0፣ 3.0፣ 3.5፣ 2.5፤ በባቲ 4.0፣ 2.6፣ 3.1፣ 3.0፤ በቡኢ 3.0፣ 3.0፣ 2.6፣ 2.0፣ 2.4፣ 3.6፤ በደብረብርሀን 3.4፣ 2.0፣ 0.4፣ -0.6፣ 0.2፣ 0፤ በዳንግላ 4.5፣ 4.5፣ 4.8፣ 4.0፣ 4.5፤ በደባርቅ 4.5፣ 4.5፤ ደብረ ማርቆስ 4.2፤ በቢሾፍቱ 4.4፣ 3.8፣ 1.0፣ 4.0፤ በእነዋሪ 4.5፤ በእምድብር 4.8፣ 4.6፤ በጅግጅጋ 4.8፣ 3.2፣ 1.8፣ 2.4፣ 0.2፣ 0.2፤ በጅማ 4.8፣ 4.8 ፤በማይጨዉ 3.2፤ በመሐል ሜዳ 3.2፣ 1.6፣ 4.2፣ 1.2፣ 0.5፤ በሮቤ 3.8፣ 4.2፣ 4.8፣ 4.0፤ በሾላ ገቢያ 3.0፣ 3.0፣ 2.1፣ 2.0፣ 2.1፣ 2.0፣ 3.0፣ 4.0፣ 3.1፤ እንዲሁም በወገል ጤና 1.8፣1.6፣ 2.2፣ 1.4፣1.8፤ በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ፡፡





**ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ**




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በአማን 3.2፣ በጂንካ 2.6፣ በማጂቴ 2፣ በማይጨዉ 1.5 እንዲሁም በኮምቦልቻ 1.4 ሚሜ የሚደርስ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ እንዲሁም አብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍል በደረቃማው የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል፡፡ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከጥቂት የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ቦታዎች በስተቀር ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025
ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ
የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጃንዋሪ ሁለተኛው አስር ቀናት ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖ እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ደረቃማ ከነበረው ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛው፣ የደቡብና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አንጻራዊ ጥንካሬ እንደነበረውና በአንዳንድ አካባቢዎችም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት ከአምስት ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ይሁን እንጂ በአመዛኙ ደረቃማ የነበረው የአየረ ሁኔታ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን በተሟላ መልኩ ለማጠናቀቅ በጎ ጎን ነበረው (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፈናቸው የጃንዋሪ ሁለተኛ አስር ቀናት ሁሉም ተፋሰሶች የበጋው ደረቅ ሁኔታ ስር እንደቆዩ የተተነተኑ የውኃ ሜቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 5) ፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ አሥራ አንድ ቀናት በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየታየ ያለው የበጋው ደረቅ፣ ጸሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6) ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን፣ በምስራቅና በደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል( ካርታ 6)፡፡ በሌላ በኩል ለዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ የተሻለ ገፅታ ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31, 2025 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመጪዎቹ የፌብርዋሪ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የመኸር ወቅት የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ላላጠናቀቁ አካባቢዎች አመቺ ሁኔታ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ለድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት የሚኖረውን ምቹ የአየር ሁኔታ በመረዳት የተሰበሰቡ ሰብሎችን አጠናቆ የመውቃትና የማጓጓዝ ስራዎችን ማከናወን ይኖርባቸዋል። በተለይም የበልግ ወቅት እርሻ እንቅስቃሴ ከመቃረቡ ጋር ተያይዞ የሰብል ማሳዎችን ከማንኛወም ተረፈ ምርት ነጻ የማድረግና ለዘር የማዘጋጀት ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል።

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣዮቹ አስራ አንድ ቀናት አብዛኛው የአፋር ደናክል፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ መረብ ጋሽ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ ባሮ አኮቦ፣ አባይ እንዲሁም የተከዜ ተፋሰሶች በደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት በላይኛው እና በመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት ላይኛው አሞ ጊቤ እና አዋሽ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ጃንዋሪ የበጋ ወቅት ማብቂያ እንዲሁም የበልግ ወቅት መሸጋገርያ ወር በመሆኑ ሊኖር የሚችለው መጠነኛ እርጥበት በጥቂቱም ቢሆን ለውኃ ሀብት መሻሻል አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et